የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 4
ADDIS ABABA 17th November, 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፬/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ለመንገድ ልማት ዘርፍ ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ከኖርዲክ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፫፻፱

CONTENTS

**Proclamation No. 474/2005**

Nordic Development Fund Credit Agreement for partly financing Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation………. Page 3309

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፬/፲፱፻፺፰

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለመንገድ ልማት ዘርፍ ድጋፍ ፕሮግራም ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል ፲ሚሊዮን ዩሮ /አሥር ሚሊዮን ዩሮ/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፫ እና ጁላይ ፲፭ ቀን ፪ሺ፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለመንገድ ልማት ዘርፍ ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ከኖርዲክ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፬/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 474/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLLIC OF ETHIOPIA AND THE NORDIC DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** a Credit Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Nordic Development Fund stipulating that the Nordic Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount not exceeding Euro 10,000,000 (ten million Euro) for partly financing Roads Sector Development Support Project, was signed in Addis Ababa on the 19th day of November 2003 and the 15th day of July, 2005;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 13th day of October, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Nordic Development Fund Credit Agreement for partly financing Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation No.474/2005."

፪. <u>ስምምነቱ ስለመፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፫ እና ጁላይ ፲፭ ቀን ፪ሺ፭ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው ቁጥር 411 የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

፫. <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ሚሊዮን ዩሮ /አሥር ሚሊዮን ዩሮ/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**2. Ratification of the Agreement**

The Credit Agreement No. 411 signed in Addis Ababa on the 19th day of November 2005 and 15th day of July, 2005 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Nordic Development Fund is ratified;

**3. power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of Euro 10,000,000 (ten million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

**4. Effective Date**

The Proclamation shall enter into force on 17th day of November , 2005.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of November, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**